ሳምንታዉ ዜና ዘገባ

ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ ራዲዮ ህዳር 27 ቀን 2001 ዓ.ም.

- እዉቁ ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ ጥፋተኛ ተብሎ 6 ዓመት እስራት እና 18 ሺህ ብር ቅጣት በወያኔዉ ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ተወሰነበት፤
- በርካታ ወጣቶች በደህንነት ታፍሰዉ ወደ ጦር ከምፕ ተወሰዱ፤ ሴቶች ማህፀናቸዉን በእርግጫ፣ ወንዶች በሽጉጥ ሰደፍ ጭንቅላታቸዉን ተደበደቡ፤
- ወያኔዎች ዛሬም በህዝብ ሀብት እየቀለዱ መሆናቸዉ ተጋለጠ፤
- ወያኔ አዳዲስ ደህንነትና ካድሬዎችን አሰልጥኖ ወደ ስራ አሰማራ፤
- በከፍተኛ ባለስልጣናት መካከል ችግር መኖሩ ተጠቆመ፤
- በርካታ የወያኔ ምክትል ሚኒስትሮች በመለስ ትዕዛዝ ከስልጣናቸዉ ተባረሩ፣ የአዲሱ ለገሠ የበረሃ ሚስቱ ታጋይ እንወይ ገ/መድህን ትገኝበታለች፤
- ምንጠራዉ አሁንም ቀጣይ መሆኑ ተነገረ፤
- የወያኔ ጄኔራሎች እርስ በእርስ በቃላት ሲወራረፉ ዋሉ ተባለ፤ በሳሞራ የኑስ ትዕዛዝ ሁሉም ሲገቡ የታጠቁትን ሽጉጥ እንዲፈቱ ተደረገ፣

የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል - ዝርዝሩን በሚቀጠለዉ ገፅ ያንብቡ …

ከስምንት ወራት በፊት ከሚያዚያ 8 ቀን 2000 ዓ. ም. ጀምሮ በሀሰትና በፈጠራ ወንጀል ሲያንከራትቱት የቆየውን እውቁ ድምፃዊ ቲዎድሮስ ካሳሁንን ጥፋተኛ ነህ ሲል የወያኔው ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ውሳኔ አስተላለፈ::

ምንም እንኩዋን ከወያኔ የሚጠበቅ በጎ ነገር እንደሌለ የታወቀ ቢሆንም ህዳር 26 ቀን ከሰዓት በሁዋላ በዋለው ችሎት ከአንድ አመት እስከ ሁለት አመት ድረስ ሊወሰንበት ይችላል ተብሎ በብዙዎች ዘንድ ተገምቶ የነበረ ቢሆንም አረመኔው የወያኔ ዳኛ ልዑል ግን ከጌቶቹ ጋር ተመሳጥሮ የስድስት ዓመት ፅኑ እስራት እና የ18 ሺህ ብር ቅጣት መወሰኑ ታውቆዋል::

ቅጣት ለማንበብ ሲታሽና ሲፈተግ የዋለው ይኸው ሴሰኛውና የትዳር ጉዋደኛውን ፈትቶ ለዓመታት ከሌላ ሴት ጋር ሲማግጥ የነበረው የወያኔ ዳኛ ተብዬ ልዑል ገ/ማሪያም በእውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ ላይ ቅጣት ከመወሰኑ በፊት «አንተን አክብረን ሳይሆን ህዝቡ ያንተን ችሎት መከታተል ስለፈለገ ብቻ ነው በትልቅ አዳራሽ ውስጥ እያስቻልን ያለነው:: ስለዚህ እንደልብህ እንድትፈነጭ አይደለም» በማለት ቲዲ አፍሮን ሲያስፈራራ ከቆየ በሁዋላ ግዳይ ጥሎ እንደመጣ ሰው በኩራት ሲጀነን እንደነበረም በችሎቱ የነበሩ ታዳሚዎች ገልፀው ቅጣቱን ካነበበ በሁዋላም ትኩር ብሎ ሲመለከተው እንደነበርም ጨምረው ገልፀዋል::

የወያኔ ቅጥረኛ ዳኛ ይህንን ዛቻ በቲዲ ላይ የሰነዘረው ህዳር 22 ቀን ከውሳኔ በሁዋላ « ከዚህ ፍርድ ቤት ሀቅ አላገኘም ፣ እግዚአብሔር ይፈርዳል!» በማለት ተናገረ ተብሎ በጋዜጣ ላይ በማንበቡ ብቻ መሆኑን ችሎቱን የተከታተሉት ታዳሚዎች ገልፀዋል::

ውሳኔ በተሰጠበት ዕለት በደህንነት እና ሲቪል በለበሱ ክትትል ፖሊሶች ችሎቱ የተሞላ ቢሆንም የቅጣት ውሳኔው እንደተሰማ እድሉን አግኝተው ጥቂት ወደ ችሎት የገቡ ዘመድ አዝማዶቹ እና አድናቂዎቹ በሚያስቅቅ ሁኔታ ሲያለቅሱ እንደነበርም በችሎቱ የተገኙት ሰዎች አስረድተዋል::

አርብ ቅጣት ይሰጣል በተባለበት ዕለት ህዝቡ ሊበጠብጥ ይችላል በሚል የፌዴራል ልዩ ኮማንዶ ጦር ከጠዋቱ 12 ሠዓት ጀምሮ ጥበቃ ማድረግ የጀመረ ሲሆን በተለይ ከሰዓት በሁዋላ ልዩ ጦር የተባለው ህዝቡ ቀድሞ ቦታ ለመያዝ ወደ ግቢ ለመግባት ቢሞክርም እየከለከለ እንደነበር የገለፁት በቦታው የነበሩ አድናቂዎቹ በርካታ ወጣቶች የዚሁ ጦር ድብደባ ሰለባ እንደሆኑም ጨምረው ገልፀዋል::

ከሜክሲኮ እስከ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል ድረስ በሶስት ዙር ጥበቃ ሲደረግ እንደነበረ የተከታተለው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን የመጀመሪያው ዙር ጀሌዎቹ የአዲስ አበባ ፖሊሶች፣ ሁለተኛው ዙር የፌዴራል ፖሊሶች ከነሙሉ ትጥቃቸው እንዲሁም ሶስተኛው ዙር ልዩ ኮማንዶ ጦር የተባለው የወያኔ ሰው አራጅ የጦር ክልፍል እንደሆነም አስረድቶዋል::

ከ15 ዓመት በላይ በህዝብ ላይ እየቀለደና እንደልቡ ፍርድ እየሰጠ ያለው የወያኔው ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም ከሁለተኛ ወንጀል ችሎት ተነስቶ እውቁ ድምፃዊ ቲዲ የተከሰሰበት ችሎት ለዚሁ ፋይል ተብሎ ተቀይሮ የመጣ መሆኑን የገለፁት የፍርድ ቤት ምንጮች ለስምንት ወራት ያህል ሲያንከራትቱት ከቆየ በሁዋላ በሰበብ አስባብ በተሳሳተና ፍፁም ሀሰት በሆነ ማስረጃ ጥፋተኛ ነህ በማለት ውሳኔ ሰኞ ህዳር 22 ቀን 2001 ዓ. ም. ሰጥቶ ቅጣቱን ለመወሰን ከአራት ቀን በሁዋላ ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ. ም. መቅጠሩ አይዘነጋም::

እውቁ የግጥምና የዜማ ደራሲ እንዲሁም ድምፃዊው ቲዎድሮስ በ1997 ዓ.ም.በተደረገው ሀገር አቀፍ ምርጫ ወቅት « በ17 መርፌ በጠቀመው ቁምጣ ...»በሚል ባወጣው አልበሙ የወያኔን ገመና በማጋለጡ እና በተገኘበት መድረክ ሁሉ ስለ አንድነት በማዜሙ ያበገነው የወያኔ ቡድን ሰበብ ፈልጎ በሌለበት የተፈጠረውን የመኪና አደጋ እንዳለ አስመስሎ በተቀናበረ የፈጠራ እና ሀሰተኛ ክስ መስርተው ለስምንት ወራት ሲያንገላቱት የቆዩ ሲሆን ህዳር 26 ቀን 2001 ዓ. ም. በዋለው ችሎት ጥፋተኛ በሚል 6 ዓመት እስራት ፅኑ እና 18 ሺህ ብር ቅጣት መወሰኑ ህዝቡን እጅግ እንዳሳዘነና ህግ በሀገሪቱ እንደሌለ በገሀድ ያረጋገጠ ነው ሲሉ የፍርድ ሂደቱን ሲከታተሉ የነበሩ አንድ የህግ ባለሙያ ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ሀሳቡን በግጥምና ዜማ በመግለፁ ብቻ ጥርስ ውስጥ የገባው እውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ በተለያዩ ሀገራት ተዘዋውሮ ባቀረበው ኮንሰርት እጅግ እውቅናን የተረፈ ከመሆኑም በላይ በኢትዮጵያዊነቱ ባለው ክብር የተነሳ ዝናን ያተረፈ ሲሆን በአንድ ወቅት በሸራተን አዲስ የዘመን መለወጫ የዋዜማ በዓልን አስመልክቶ ዝግጅቱን እንዲያቀርብ ከተስማማ በሁዋላ የሚያቀርባቸው ዘፈኖች ግን ተመርጠው መሆን እንዳለበት ሲነገረው በነፃነት የፈለኩትን መጫወት ካልቻልኩ በሚል የተከፈለውን ገንዘብ መልሶ የተፈራረመውን ውል ቀድዶ ወደ ውጭ ሀገር ተጉዞ በዓመት በዓሉ ዋዜማ በውጭ ሀገር ስራዎቹን ማቅረብ መቻሉ ያበገናቸውና « ንቆን ነው» በሚል የተበሳጬት እነ ሼህ አላሙዲን ጥርስ ውስጥ የገባበት አጋጣሚ እንደነበር ያስተወሰው ዘገባ በሌላ ጊዜም የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ባለቤት ወ/ሮ አዜብ መስፍን በሸራተን አዲስ አንድ ዝግጅት አዘጋጅታ በዕለቱ እንዲገኝላት ጥሪ ብታቀርብለትም ሌላ ፕሮግራም እንዳለበት በመግለፅ እንደማይገኝ የነገራት ሲሆን ሌሎች ድምጻዊ የተገኙላት ቢሆንም እሱዋም እንደሼሁ ሁሉ «ንቆኝ ነው» በማለት ቂም የያዘችበት መሆኑን ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል::

ከወያኔ ቡድን በተጨማሪ በሁለቱ ግለሰቦች ቂም የተቋዋጠረበት እውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ በነሚሚ ስብሀቱና በነ ሰለሞን አስመላሽ ተላላኪነት ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ሲሩዋሩዋጡ ከርመው ፍፁም ሀሰት በሆነ መንገድ ተጠልፎ የተያዘ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆ ከ8 ወራት በላይ አሰቃይተው ጥፋተኛ ነህ በማለት 6 ዓመት እስራት እና 18 ሺህ ብር ቅጣት መፍረዳቸው አሳዛኝና አሳፋሪ መሆኑን ገልፆዋል::

ሚያዚያ 8 ቀን 2000 ዓ. ም . እንደዋዛ ወደ ፍርድ ቤት የሔደው ቲዲ በዚያኑ እለት በተከፈተበት ፋይል የዋስትና መብት በመከልከል ለእስር ተዳርጎ የቀረ መሆኑን እና እስከ ዛሬም ድረስ ያልተፈታ ከመሆኑም በተጨማሪ በወያኔው ቀንደኛ ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያም የ6 ዓመት ፅኑ እስራት እና 18 ሺህ ብር እንዲቀጣ መወሰኑ የሀገሪቱን ህዝቦች ያበሳጨ መሆኑም ታውቆዋል::

በተለይ ጥቅምት 24 ቀን ባስቻለው ችሎት ይኸው አረመኔ ዳኛ ልዑል የማያዳግም ውሳኔ እሰጣለሁ በሚል ለህዳር 22 ቀን 2001 ዓ. ም. ተለዋጭ ቀጠሮ ሰጥቶ የነበረ ሲሆን ባለውም መሰረት የተሰጠውን ተልዕኮና ግዳጅ ለመወጣት ሲል ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ እንዲሉ ቲዲ በሌለበትና በሀገር ውስጥ ባልነበረበት ማስረጃ አሰባስበናል በሚል ያጠራቀሙትን ሀሰተኛ ና የፈጠራ ድሪቶ ታሪክ እውነተኛ ነው ብሎ አይኑን በጨው ታጥቦ ህዳር 22 ቀን ጥፋተኛ ነው ብሎ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን ችሎቱን የተከታተሉ ወገኖች ገልፀው፤ በእለቱ ይኸው አረመኔ ዳኛ ውሸት መሆኑን እያወቀ እውነት አስመስሎ ቢያነበንብም እንደ ጌታው መለስ ዜናዊ የአምቦ ይሁን የጦሳ ውሀ አሁንም አሁንም እየተጎነጨ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሻይ እረፍት አድርገን እንመለሳለን እያለ እየተርበተበተ ከ8 ሰዓት ጀምሮ እስከ 10 ሰዓት ከ30 ድረስ እየታሸ መቆየቱንም ጨምረው ገልፀዋል::

በመጨረሻም በደከመ ድምፅ እውቁ ድምጻዊ ጥፋተኛ መሆኑን ሲገልፅ በችሎቱ ውስጥ የነበረው ታዳሚ በሙሉ እርስ በርስ እየተቃቀፉ አንገታቸውን ደፍተው በእንባ ሲራጩ እንደነበረም ታውቆዋል::

ችሎቱ ተጠናቅቆ ሲበተንም ከችሎት ውስጥ እና ከውጭ በነበሩ የቲዲ አድናቂና ቤተሰቦች ላይ የትግርኛ ተናጋሪ የሆኑ ደህንነት ሰራተኞች እጅግ ዘግናኝ ድብደባ ከመፈፀማቸውም በላይ ለጊዜው ቁጥራቸው ያልታወቁ ወጣቶች ታፍሰው ልደታ ቤተክርስቲያን አቅራቢያ በሚገኘው የፌዴራል ፖሊስ ካምፕ ውስጥ እንዳጎሩዋቸው ታውቆዋል::

ሴቶችን ማህፀናቸውን በእርግጫ እና ፀጉራቸውን እየቦጨቁ መሬት ለመሬት ሲጎትቱዋቸው ወንዶችን ደግሞ አንዳንዶቹን በቦክስ ሌሎቹን በሽጉጥ ሰደፍ ሲቀጠቅጡዋቸው እንደነበረ በቦታው የነበሩ የአይን እማኞች ገልፀዋል::

ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሀገሩ በነፃነት እንዳይኖር ገደብ የጣለው የወያኔው ቡድን በሌሎች ብሔር ተወላጆች የደህንነት አባላት ላይ ስለማይተማመን ከትግራይ ክልል ምንም አማርኛ ቁዋንቁዋ መናገር የማይችሉትን መልምሎ እና አሰልጥኖ ወደ ስራ ያሰማራቸው ሲሆን እነዚሁ ደናቁርት አዲስ የደህንነት አባሎች አድርጉ የተባሉትን ከመፈፀም ሌላ አንዳችም ርህራሄ የሌላቸው መሆኑን በቲዲ አፍሮ የፍርድ ዕለት ያሳዩ አረመኔዎች ናቸው ሲል የደረሰን ዘገባ ያስረዳል::

የተሰረዘና የተደለዘ ሀሰተኛ የሰውና የሰነድ ማስረጃ ያቀረበው የወያኔ ቡድን አረመኔውን ዳኛ ልዑል ገ/ማሪያምን ለአንድ ወር ቀይሮት የነበረ ቢሆንም አዝማሚያውን ሲያይና ክሱ ፍሬ ቢስ መሆኑን ሲረዳ እራሱ እንዳቦካው እራሱ እንዲጋግረው ከሄደበት ችሎት አምጥተው

ተመልሶ የቲዲ ፋይል የሚታይበት ችሎት እንዲመደብ የተደረገ መሆኑን የገለፁት የፍርድ ቤት ምንጮች እውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ የቀረበበትን ክስ ከበቂ በላይ ምስክሮችን አቅርቦ ያስመሰከረ እና የሰነድ ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም የምስክሮቹን ቃል እና ማስረጃውን ውድቅ አድርጎ ለአንድ ወር ከተዛወረበት ሲመለስ ጥፋተኛ በማለት ውሳኔ እንደሰጠው አጋልጠዋል::

እውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን ህዳር 22ቀን 2001 ዓ. ም. ከመቼውም ጊዜ በላይ ተረጋግቶ የቀረበበት ዕለት ሲሆን ችሎቱ 8 ሰዓት ላይ ተሰይሞ 10 ሰዓት ከ30 ደቂቃ ላይ እስኪጠናቀቅ ድረስ ቆይቶ « ጥፋተኛ ነህ» ብሎ የወያኔው ዳኛ ፍርድ ከሰጠ በሁዋላ የጥፋት ማቅለያ ሀሳብ እንዲያቀርብ ቢጠየቅም «እግዚአብሔር ፍርድ ይሰጣል! »በማለት የተናገረ ሲሆን ጠበቃው አቶ አምሀ በልሁ የተባለውም ቲዲ ጥፋተኛ ስላልሆነ የማቅለያ ሀሳብ አንሰጥም የለንም በማለት ምላሽ የሰጠ መሆኑንና ዳኛው በለሆሳስ ድምፅ «ይሄ ጥጋብ ነው» ነው በማለት በብስጭት እያጉተመተመ ፋይሉን ሲወረውረው መታየቱን በችሎቱ ውስጥ የነበሩ የዓይን እማኞች ገልፀዋል::

ህዝብ ለምን ወደደው ስለሀገርና ስለ ስለህዝብ አንድነት ለምን ዘፈነ እያሉ የሚበግኑት የወያኔ ቡድን አባላት በጅማ ለዘመናት ተዋድዶና ተፋቅሮ የኖረውን ህዝብ እነሱ በፈጠሩት ተንኮልና ሸር የእስልምና እና የክርስትና እምነት አማኞች እርስ በርስ እንዲጋጩ አድርገው ብዙ የሰው ህይወት ያለፈ ቢሆንም እውቁ ድምፃዊ ቲዲ አፍሮ በጅማ ከተማ ስታዲየም ውስጥ ባዘጋጀው ኮንሰርት ላይ ***« ተዋድዶ የኖረው እስላም ክርስቲያኑ፤ ተዘነጋሽ እንዴ ኢትዮጵያ መሆኑ*** »እያለ በማዜም ወያኔ ፈጥሮት የነበረውን መቃቃር በአንድ ቀን ሽሮ የመጣ መሆኑን ያወቁት እነዚሁ አረመኔዎች በንዴትና በብስጭት ባህር ዳር ከተማ ቀጣይ የነበረውን ፕሮግራም እንደሰረዙበት ያስታወሱት ወገኖች በአሁኑ ሰዓት በጅማ ከተማ እና አካባቢዋ እጅግ ከፍተኛ ተወዳጅነትን ያተረፈ መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

በሰሩት ወንጀል ሁሌ ስጋትና ጭንቀት የማይለያቸው የወያኔ ቡድን በጅማና በሌሎችም የሀገሪቱ ክፍሎች ያገኘውን የህዝብ ፍቅርና ክብር በመፍራት ወደፊት በኛ ላይ ታሪክ ሊሰራ ይችላል በሚል ፍራቻ ፍፁም ሀሰት በሆነ መንገድ ክስ መስርተውበት ለዚህ የዳረጉት መሆኑንም ለቲዲ አፍሮ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ገልፀዋል::

ህዳር 14 ቀን 2001 ዓ.ም.በታላቁ ሩጫ ላይ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ ሲቀርብ የነበረው የእውቁ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን መታሰርን በመቃወም መሆኑን የተረዱት ወያኔዎች የደህንነት ሰራተኞቹን አሰማርተው ወጣቱን ሲደበድቡና እና ሲያሰቃዩት እንደነበረ አይዘነጋም::

በሀገር እና በህዝብ ላይ እየቀለደ ለ17 ዓመታት ያሸፈው የወያኔ ቡድን ዘንድሮም እድሜውን ለማራዘም ሲል እንደ አዲስ ከትግራይ የደህንነት ሰራተኞችን በድብቅ እየመለመለ አሰልጥኖ ያመጣ መሆኑን የደህንነት ቢሮ ምንጮች ገልፀዋል::

ከ4 ወር በፊት የአካል ብቃት ኮርስ የተሰጣቸው እነዚሁ የህወሀት አባሎች በስውር አዲስ አበባ ውስጥ ሰልጥነው ወደ ስራ የተመደቡ ሲሆን፤ አማርኛ ቋንቋዋ ቢሰሙም መናገር የማይችሉ በመሆኑ በቀላሉ ከሌሎቹ ለመለየት እንደሚቻሉ የገለፁት ምንጮቹ በተለይ በታላቁ ሩጫ ላይና ቲዲ አፍሮ ፍርድ ቤት በቀረበባቸው ቀናቶች ሲያሳዩ የነበሩት ሁኔታዎች በእጅጉ አሳዛኝ እንደነበረ አስረድተዋል::

ህዝቡ በኑሮ ውድነት ተወጥሮ ፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችን በርሀብ እየተሰቃዩ፤በነዳጅ ዋጋ የስንግ ተይዞ ባለበት በዚህ ወቅት ወያኔ እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ ከፍተኛ የሀገር ገንዘብ ወጪ አድርጎ የህወሀት አባል የሆኑ ደህንነቶችን መልምሎና አሰልጥኖ ህዝብን እንዲያፍኑ ፤ህዝብን እንዲረግጡ ማሰማራቱ ለህዝቡ ካለው ንቀትና ጥላቻ የመነጨ ብቻ ሳይሆን ህዝብን በመፍራቱ ጭምር መሆኑን የደህንነት ምንጮች ገልፀዋል::

ለብዙ ዘመናት በደህንነት ስራ ላይ ተሰማርተው በህዝብ ላይ በደል ሲፈፅሙና ከህዝብ ጋር እሳትና ጭድ የሆኑትን ነባር የሌላ ብሔር ተወላጆችን እነ መለስ ከጊዜ ወደ ጊዜ እምነት እያጡባቸው በመሆኑ ከትግራይ የህወሀትን አባል ብቻ የሆኑትን ወጣቶች ከፍተኛ ገንዘብ ወጪ በመመደብ መልምለው እና አሰልጥነው በማሰማራታቸው ነባሮቹ አኩርፈው እንደሚገኙም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው እንዲሉ ነባር የደህንነት ሰራተኞቹን ለይስሙላ እንደ አለቃ በየምድቡ ያስቀመጡዋቸው ቢሆንም በተመደቡበት ቦታ ምንም የማዘዝም ሆነ የመስራት ስልጣን እንደሌላቸው የገለፁት ምንጮቹ በአሁኑ ሰዓት እነ መለስ ዜናዊ ትልቁን ስራ እያስሰሩ ያሉት እና እምነት የጣሉባቸው በአዲሶቹ የደህንነት ሰራተኞች ላይ ሲሆን፤
« በአዲስ ጉልበት ባልተበረዘ አእምሮ ትሰራላችሁ ብለን እናምናለን» ብለው እነመለስ ገደል ግቡ ሲሉዋቸው የሚሽቀዳደሙ መሆናቸውንም ጨምረው አስረድተዋል::

በአዲሶቹ እና በነባሮቹ የደህንነት አባሎች መሀከል መግባባት ጠፍቶ እንዲያውም መናናቁ ጎልቶ እየወጣ መሆኑን የገለፁት ምንጮቹ አዲሶቹ « የመለስ ልጆች »የሚል ቅፅል ስም እንደወጣላቸው እና የእርስ በርሱ ጥላቻ እንደተስፋፋ አብራርተዋል::በዚህም የተነሳ በቅርቡ በደህንነት ሰራተኞች መሀከል ግምገማ በሚል ነባሮቹን የመመንጠር ስራ ሊሰራ ይችላል ሲሉም ምንጮቹ ግምታቸውን ሰንዝረዋል::

በችግር ላይ ችግር እየደራረበ የችግር ድሪቶ ተከናንቦ ያለው ወያኔ ችግሬን ይቀርፉልኛል በሚል ከደህንነቶቹ በተጨማሪ ሰሞኑን በተለያዩ ክልሎች አዳዲስ ካድሬዎችን አሰልጥኖ ወደ ስራ እያሰማራ መሆኑ ታወቀ::

በትግራይ ክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተመልምለውና ሰልጥነው ወደ ስራ ላይ የተመደቡት አፍለኛ የወያኔ ካድሬዎች ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ከመሆኑም ባሻገር ባለስልጣናቱ ለቁጥጥር እንኳዋን እንደተቸገሩ ከተለያየ አካባቢ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በትግራይ  ከሁለት ወራት በላይ በመቀሌ የፖለቲካ ትምህርት ሲሰጣቸው የቆዩት እነዚሁ የህወሀት አባሎችና  አዳዲስ  ካድሬዎች በአብዛኛው ከትምህርት ቤት የተመለመሉ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በተለይ የዩኒቨርስቲ ተመራቂ የሆኑ ስራ አጥተው የተቀመጡ ወጣቶች ብዙ እድል እንደሚሰጣቸው ቃል የተገባላቸው ከመሆኑም ባሻገር ይህንን ኃላፊነት ተቀብለው  ካልሰሩ በኢትዮጵያ ውስጥ ስራ ማግኘት እንደማይችሉ በግልጽ ተነግሮዋቸው እንደገቡ ዘገባው አብራርቶዋል::

ከ4500 በላይ በአንድ ዙር ወጣቶችን ለሁለት ወር  መቀሌ  በሚገኘው የሰማዕታት አዳራሽ  በተባለው ውስጥ የፖለቲካ ትምህርት ሲሰጣቸው ከቆየ በሁዋላ ባለፈው ሳምንት የተመረቁ ሲሆን በዚህም ወቅት የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ለተመራቂዎቹ በእስክሪን አዲስ አበባ ሆኖ መቀሌ ለተመረቁት ማሳሰቢያ እንደሰጠም ዘገባው ገልፆዋል::

መለስ በሰጠው በዚሁ ማሳሰቢያ ላይ ድርጅቱ ከገባበት የፖለቲካ  ኪሳራ የምታላቅቁት እናንተ መሆናችሁን ተገንዝባችሁ የተሰጣችሁን ኃላፊነትንም  እንድትወጡ አደራ እላለሁ እያለ ደጋግሞ ሲማጸናቸው ተደምጦዋል ያለው ዘገባ ከእንግዲህ ወዲያ ስልጣን የናንተ ሊሆን እንደሚችልም ላስገነዝባችሁና ተግታችሁ እንድትሰሩ  እወዳለሁ እያለ ቃለ መሀላ የፈፀመ ይመስል ደጋግሞ ሲወተውት እንደነበረ ዘገባው አስረድቶዋል::

በተመሳሳይ ከአዲስ አበባ ከተማም ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው ስራ አጥተው የተቀመጡና ገና የተመረቁ ፍረሽ ወጣቶችን  በግዴታ አባል አድርገው  ለካድሬነት መልምለው ሻሸመኔ በሚገኘው አላጌ የግብርና ኮሌጅ ለ15 ቀናት የፖለቲካ ትምህርት ሲሰጣቸው የቆዩ 1200 አፍለኛ ካድሬዎችን ያስመረቀ መሆኑን እና በአራት ዙር ከ6 ሺህ በላይ እንደተመረቁም  ይኸው የደረሰን ዘገባ ገልፆ ከዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በተጨማሪ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም አባል  ካድሬዎች ሆነው መመልመላቸውና ኮርስ እንዲወስዱ መደረጉን አስረድቶዋል::

ወጣቶቹ  ከአላጌ ግብርና ኮሌጅ ተመርቀው  ከመጡ በሁዋላ በቀበሌ ደረጃ የተመደቡ ሲሆን ደመወዛቸው ከ1 ሺህ 500 ብር በላይ እንደሆነላቸው የገለፀው ዘገባ ቀድመው የወያኔ ዕጩ ሆነው  ብቻቸውን ተወዳድረው አሸነፉ የተባሉት ካድሬዎች እየተባረሩ በምትካቸው አዳዲሶቹ እንደገቡበት ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

ወያኔ አሁንም ስልጣኑን የሙጥኝ ብሎ በያዘው መንገድ ለመቀጠል  ካለው ምኞት የተነሳ ነባሮቹን እያባረረ አዳዲስ እና አፍለኛ  ካድሬዎቹን በጥቅም እና በማስፈራራት በየቀበሌው የመደበ መሆኑን የገለፀው የደረሰን ዘገባ በአንድ ቀበሌ ውስጥ ከ30 በላይ እንደተመደቡና የደህንነት ስራም በተጨማሪ እንዲያከናውኑ መመሪያ እንደተሰጣቸው ዘገባው ገልፆዋል::

በተለይ በነሐሴ ወር ውስጥ አራቱም የወያኔ ድርጅቶች በተለያዩ ከተሞች በተናጠል ስብሰባ ባደረጉበት ወቅት አዳዲስ  ካድሬዎች ቦታ ይሰጣቸው በሚል ከፍተኛ ሙግት ውስጥ እንደነበሩ ያስታውሰው ዘገባ ከህወሀት አርከበ እቁባይ ፤ ከብአዴን ተፈራ ዋልዋ ጥያቄ ያቀረቡ

ሲሆን፤ ከኦህዴድና ከደኢህዴንም ካድሬዎች ተመሳሳይ ጥያቄ ቀርቦ እርስ በርስ ሲያጨቃጭቃቸው የነበረ ቢሆንም ይኸው ጭቅጭቅና ንትርክ አዋሳ ከተማ አንድ ላይ የወያኔ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች ለ5 ቀናት ባደረጉት ጉባዔ ላይም ይኸው አጀንዳ ቀርቦ ሲያከራክራቸው እንደነበረ ያስታውሰው ዘገባ በተለይ ተፈራ ዋልዋ « ለአዲስ ተተኪ ትውልድ አባሎቻችን ስልጣን ልናስረክባቸው ግድ ይለናል » እያለ ሲወተውት እንደነበርና በዚህም ምክንያት የተነሳ ከመለስ ዜናዊ ጋር ከፍተኛ ንትርክ ውስጥ ገብቶ እንደሚገኝ ዘገባው አብራርቶዋል::

በተፈራ ዋልዋና በመለስ ዜናዊ መሀከል የተጀመረው ወጣቶች ይተኩ የሚለው ንትርክ ወደ ሌሎች ካድሬዎችም ተስፋፍቶ በእንጥልጥል እንደነበረ እና አሁን መለስ መላው ሲጠፋው ምንም የፖለቲካ እውቀት የሌላቸውን ከየትምህርት ቤቱ ሰብስቦ የካድሬነት ፀበል እያጠመቀ በጉባዔው ላይ ለተጠየቅኩት ጥያቄ ምላሽ እየሰጠሁ ነው በማለት ደፋ ቀና እያለ መሆኑንም ዘገባው አስረድቶዋል::

መለስ በስልጣን ላይ ለመቆየት ካለው ፍላጎት የተነሳ በወያኔ ትውልድ ገዳይ በሆነ የትምህርት ፖሊሲ ውስጥ ተምረው የወጡ ምንም ሀገራዊ ራዕይ የሌላቸው ወጣቶችን ሰብስቦ ስልጣን ተረካቢ ናችሁ እያለ እያጃጃላቸው እንደሚገኝ የገለፀው ዘገባ በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የተጀመረው ሽኩቻ ይዘቱና መጠኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፋና እያደገ በመምጣት ላይ መሆኑን ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

በወያኔ ውስጥ የተጀመረው ሽኩቻ ተባብሶ ወደ ምንጠራ የተሸጋገረ ሲሆን ሰሞኑን በርካታ ምክትል የሚኒስትሮች ከስልጣናቸው እንደተባረሩም ለማወቅ ተችሎዋል:: የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የኔን ቡድን አይደግፉም ያላቸውን ሚኒስትሮች ከአንድ ወር በፊት የመነጠራቸው ሲሆን ሰሞኑን ደግሞ ምክትል ሚኒስትሮቹን እያጨደ መሆኑን የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በመለስ ፊርማ የተባረሩት እነዚሁ ሚኒስትር ደኤታዎች ወይም ምክትል ሚኒስትሮች ከበረሀ የመጡትንም ቢሆን ያልተወ ሲሆን ከነዚህም መሀከል በረሀ እያሉ የአዲሱ ለገሰ ሚስት እና የሁለት ልጆቹ እናት እንደሆነች የሚነገርላት ቀድሞ የፀረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበረችውና አሁን የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ዳይሬክተር የነበረችው ወ/ሮ እንወይ ገ/መድህን የምትገኝበት መሆኑንም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ያልበላቸውን እያከኩ የኖሩት እነዚሁ የወያኔ ባለስልጣናት አንድም ቀን በራሳቸው ኃላፊነት ውሳኔ ሳይሰጡ በስማ በለው ሲጉዋዙ የነበሩ የፍትህ ሚኒስትር ደኤታዎች ወ/ሮ ስመኝ ውቤና ዶክተር ሀሺም ቶፊቅ ፤ከሴቶች ጉዳይ ሚኒስትር ወ/ሮ ኡባህ መሐመድ፤ ከፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቲር አቶ ምዕረት ሃብተማሪያም ፤ከማስታወቂያ ሚኒስቲር አቶ ተሰማ ፎቲ እና ሌሎችም ምክትል ሚኒስትሮች ከስራቸው የተባረሩ መሆኑን ዘገባው አብራርቶዋል::

እነዚሁ ተባራሪ ምክትል ሚኒስትሮች ከ1 ወር በፊት አለቆቻቸው ከስልጣናቸው ተነስተው የተባረሩ መሆኑን ያስታወሰው ዘገባው ዛሬ ደግሞ ምክትሎቹ እጣው ደርሶዋቸው በእርግጫ ተብለው እንደ አልባሌ እንደተጣሉ ዘገባው ገልጾዋል::

ለተባረሩት ምክትል ሚኒስትሮች እንዳያማህ ጥራው እንዳይበላ ግፋው እንዲሉ «እስከ ዛሬ ላበረከታችሁት አስተዋፅኦ ምስጋና ይገባችሁዋል» የሚል ብጣሽ ወረቀት በወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ የተፃፈላቸው ሲሆን ከህዳር 17 ቀን 2001 ዓ. ም. ጀምሮ ስራቸውን ለቅቀው እንዲወጡ የሚያስገድድ መሆኑንም ዘገባው ጨምሮ አስረድቶዋል::

በውስጥም በውጭም የስንግ የተወጠረው የመለስ ዜናዊ ቡድን መተንፈሻ ጊዜ አገኛለሁ በሚል የራሴ ናቸው እያለ ሲያወድሳቸውና ሲያሞካሻቸው እንዳልነበረ ዛሬ እንደ አሮጌ ቁና በአየር ላይ እያንሳፈፈ እያባረራቸው ሲሆን በቀጣይም ሌሎች ሚኒስትሮችና ምክትል ሚኒስትሮች ባለተራዎች እንዳሉ ዘገባው አጋልጦዋል::

በአሁኑ ሰዓት በሱማሌ ጉዳይ የወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት እርስ በርስ እየተነታረኩ ሲሆን ንትርኩ ወደ ጦር አለቆች ተዛምቶ የቃላት መወራወር ደረጃ ደርሶ በየጊዜው ስብሰባ በሚል ያለ አንዳች ስራ እየተጎለቱ እንደሚውሉ ከመከላከያ የውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ዘገባ ገለፀ::

የወያኔ የጦር ጄኔራሎች ሰሞኑን በመኮንኖች አዳራሽ ውስጥ ለ7 ሰዓታት የፈጀ ንትርክ ያካሄዱ ሲሆን የስብሰባው ዋና አላማ በመኮንኖቹ መሀከል ተነስቶ የነበረው የሱማሊያ ጉዳይ እንደነበረም ምንጮቹ ገልፀዋል::

ረቡዕ ህዳር 24 ቀን 2001 ዓ. ም. ከጠዋቱ 3 ሰዓት ጀምሮ ለምሳና ለሻይ እረፍት እያለ እስከ 11 ሰዓት ድረስ የቆየ መሆኑንና በዕለቱ መኮንኖቹ ለሁለት ተከፍለው በቃላት ሲዋቀጡ እንደዋሉም የምንጮቹ ዘገባ አብራርቶዋል::

ስብሰባው የተመራው በወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ቀኝ እጅ በሆነው ጄ/ል ሳሞራ የኑስ መሆኑን የገለጹት ምንጮቹ ሁሉም መኮንኖች የክብር ልብስ ለብሰው እንዲመጡ ትዕዛዝ የሰጠ ቢሆንም አንዳንዶቹ የመስክ ልብስ ለብሰው በመምጣት ተቃውሞአቸውን የገለፁ ሲሆን በጄኔራሎቹ መሀከል መተማመን ስለጠፋ ወደ ስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ሲገቡ የታጠቁትን ሽጉጥ በር ላይ ለሚጠብቁ ወታደሮች አስረክበው እንዲገቡ መደረጉን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ጦሩ ወደ ሱማሊያ ሲገባ ተቃውመውን ነበር:: ነገር ግን ወታደር የታዘዘውን ይፈፅማል እንጅ ንትርክ ውስጥ አይገባም ብላችሁ ነበር:: የመጀመሪያውን ግዳጅ ከፈፀመ በሁዋላ ወደ ድንበር ላይ ይመለስና ይስፈር ብለን ስንናገር አድማጭ ከማጣታችንም በላይ የሚያሸማቅቅ ምላሽ ተሰጥቶናል::ዛሬም ጦሩ መግቢያ መውጫ አጥቶ ተወጥሮ ችግር ውስጥ ገብቶ በየቀኑ እየሞተ እና የሀገር ሀብት እየደቀቀ መሆኑ እየታወቀ ተጠያቂው ማን ሊሆን ነው? በማለት ስማቸው ያልተጠቀሰ ጄነራል መኮንን ጥያቄ ያነሱ ሲሆን በዚህ ንግግር የተደናገጠው

ሳሞራ የኑስ « ይህን ለወደፊት በስፋት ግምገማ የምናደርግበት ሲሆን ዋነኛ ፍሬ ነገሩ ግን ወታደር መሆናችንን መዘንጋት የለብንም ። የታዘዝነውን መፈፀም እንዳለብን ለአፍታም መርሳት የለብንም» ካለ በሁዋላ ህገ መንግስቱን መጠበቅ የእኛ ኃላፊነት መሆኑን የሚዘነጋ ያለ አይመስለኝም በማለት አስፈራርቶ ሀሳብ ለማስቀየር ቢሞክርም ሁሉም ሳይስማሙ በመቅረታቸው ስብሰባና ንትርኩ ያለ ውጤት ሊበተን እንደቻለ ምንጮቹ በዝርዝር አስረድተዋል።